# በኦስትሪያ-ቪዬና ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን በአገራቸው ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ተወያዩ

በኦስትሪያ ነዋሪ የሆኑ እና ቁጥራቸው ከሀምሣ በላይ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን እ.ኤ.አ. ሴፕቴምበር 26 ቀን 2014 በቪዬና ከተማ የተ.መ.ድ ጽ/ቤት በመሰባሰብ በአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ተወያዩ፡፡ አገራችን በአሁኑ ወቅት በእርሻ፣ በኢንዱስትሪ፣ በመሰረተ-ልማት ዝርጋታ፣ በማህበራዊ ዘርፎች ዙሪያ እያስመዘገበችው ያለውን አንፀባራቂ ውጤት የሚሊንየም ግቦችን በማሳካት በአጭር ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ በመሰለፍ ሩቅ በማይባል ጊዜ ደግሞ ከፍተኛ ገቢ ካለው ማህበረሰብ ለመድረስ የተጀመረውን ጉዞ እውን እንደሚሆን ማሳያ እንደሆነበጀኔቫ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት የዲያስፖራ ጉዳዮች አስተባባሪ የሆኑት አቶ ረዳኢ ግርማይ በዝርዝር አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ እና የሚገኝበት ደረጃ፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ዲያስፖራ ፖሊሲ እና ጠቀሜታው፣ ሚሲዮኑ ለማህበረሰቡ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች በተመለከተ በዝርዝር በማንሳት ውይይት ተደርጓል፡፡ ከኢትዮጵያውያኑ በተነሱ ጥያቄዎች ላይ በመወያየት የጋራ ግንዛቤ መያዝ ተችሏል፡፡ በተለይም የህግ የበላይነት ባልተከበረበት ሁኔታ በአገራችን የሚፈለገውን የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እውን ለማድረግ እንደሚያስቸግር ግንዛቤ ተይዟል፡፡ በመጨረሻም የአገራቸውን ዕድገት መመኘት ብቻ ሳይሆን በአገራቸው እድገት ላይ ተዋናይ ለመሆን ተደራጅተው ለመንቀሳቀስ ተሰማምተዋል፡፡ ተሳትፎአቸውን አጠናክረው ለመቀጠል የኮሚኒቲ አስተባባሪ አባላትን በመምረጥ ለአገራቸው ያላቸውን ድጋፍ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ቃል ገብተዋል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለም የኢትዮጵያ መንግሥት በኦስትሪያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ እንዲከፈት ያላቸውን ጽኑ ምኞት ገልፀዋል፡፡ መንግሥት የህብረተሰቡን ፍላጐት እና የአገራችንን ጥቅም ማዕከል በማድረግ ለህብረተሰቡ ጥያቄ ምላሽ እንደሚሰጥ ተገጾላቸዋል፡፡